# ቀስተ ደመና

የሰላምና የወድማማችነት ድምፅ ሬድዮ ጋዜጣ

ቁጥር 4- 6 ታህሣሥ / የካቲት 1990

## ከአዘጋጅ ብዕር

የቀስተ ደመና ሬዲዮ፤ የሰላምና የወንድማማችነት ድምፅ ሥርጭቱን የጀመረው መስከረም 1 ቀን 1990 ዓ ም ነው።

ይህ ሁለተኛ መጽሄት የሚቀርበው ሬዲዮው ከጀመረ ከስድስተኛው ወር በኋላ ስለሆነ በቅርቡ ከተላለፉትና ባጭሩ ከቀረቡት የተወሰኑ ዜናዎች ሌላ፤ የመጽሄቱ ዋና ይዘት ለሃገራችን ወቅታዊ ጉዳዮችና ጥያቄዎች ቅድሚያ ትኩረት ለሰጡ ትችቶች፤ ትንተናዎች ወዘተ ነው።

መልካም ንባብ !

* ክሊንተን አፍሪካ........................1
* የፖለቲካ አጥቂነት.....................2
* በአንድ ራስ አንድ ምላስ.........3
* ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ኬንያ.......5
* የእብዶች ሉጂክ ........................6
* በ 1992ቱ ምርጫ ላይ
  የተጠነሰሰው ሤራ.....................7
* ህወሀት ለምርጫ ይዘጋጃል፤
  ተቃዋሚዎችስ?........................8
* የወያኔ መሰንበቻ ስልት...........10
* ከጋዜጦች አምድ.................... 11
* ዘመናዊ ባርነት...................... 15
* የወያኔን ኢትዮጵያ
  ሾላ በድፍን.........................17

ቀስተ ደመና (Radio Rainbow) የሰላምና የውንድማማችነት ድምፅ ሬዲዮ
በአጭር ሞገድ(short wave) እንደሚከተለው ይተላለፋል ፤

| ቀን | ሞገድ | ሰዓት | አቅጣጫ |
|---|---|---|---|
| ሐሙስ | 19 ሜትር ባንድ<br>15.365HZ | በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር<br>ከምሽቱ 1 እስከ 2 ሰዓት | ምስራቅ አፍሪካ<br>ኢትዮጵያ |
| ዓርብ | 31 ሜትር ባንድ<br>9855kHz | በአሜሪካ ሰዓት አቆጣጠር<br>9.00p.m. - 10.00pm | ሰሜን አሜሪካ<br>ምስራቃዊ ጠረፍ |
| እሁድ | 49 ሜትር ባንድ<br>5.910kHz | በአውሮፓ ሰዓት አቆጣጠር<br>9.00a.m-10.00am (10.00-11.00a.m ለብሪታንያ ) | ምዕራብ አውሮፓ |

አድራሻችን፤
አስተያየት፤
ትችት፤ ወዘተ
ካላችሁ,

Radio Rainbow ,
c/o P.O .Box 140104
53056 Bonn , Germany
Fax : 0049 228 612381

GRAPECA ሰኢአቀ RAGPEHA
Groupe de Recherche et d'Action pour la paix en Ethiopie et dans la Corne de l' Afrique
Research and Action Group for peace in Ethiopia and the Horn of Africa
ሰላም ለኢትዮጵያና አፍሪካ ቀንድ የምርምርና የተግባር ቡድን

አነስተኛና ትዓማኒነት ያለው አማራጭ ይዞ በኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ በዓለም አቀፍ ኮሚኒቲ ፊት መቅረብ ማለት ነው።

ሁለተኛ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ዘመቻ ሲባል አሁን እንደተያዘው ሁሉም በተናጥል እየዞረ የራሱን መፍትሄ፣ የራሱን ትግል፣ ሁሉም በተናጠል በራሱ ላይ የሚሰነዘረውን ጭቆና መቃዎምና ማጋለጥ አይደለም። ተቃዋሚ ሁሉ አራምደዋለሁ ከሚለው ፖለቲካ የጋራ የሆነውን አነስተኛ ዓላማ በጋራ ይዞ በኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ በዓለም አቀፍ ኮሚኒቲ ፊት የጋራ አማራጭ ይዞ ለሱ በጋራ መታገል ማለት ነው።

**ባጭሩ ተቃውሞ ማሰማትና ማጋለጥ ብቻ ሳይሆን አማራጭ ማቅረብ። አማራጭ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን ይህን አማራጭ ይዞ በጋራ መንቀሳቀስ። ይህ ካልሆነ ምን ያህል ላይና ታች ቢባል ትግሉ ፈቀቅ አይልም። ይህ ከተደረገ ግን ከወያኔ አንጻር ሊውጠው ሊተፋው የማይችለው አቋም ይዘን እንቆማለን። የኢትዮጵያ ሕዝብም የትግል ወኔ ይቀሰቀሳል። አሉታዊ ብቻ ናቸው፤ አማራጭ ብናጣ ኢህአዴግን ለመደገፍ ተገደድን የሚሉትን ባእዳንም ይህንን አሳዛኝ ፌዛቸውን ትተው ቆም ብለው እንዲያስቡ እናደርጋቸዋለን። ይህ ሁሉ ሲሆን ደግሞ በዚያው ልክ ለዚች አገራችን ሰላምና ዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል ግልጽ ዓላማና አቅጣጫ ሰጥተነዋልና ያማይቀረው የድል ቀን ይፋጠናል ማለት ነው።**

......................////....................

# በአንድ ራስ አንድ ምላስ እንዲሆኑ

በሃገራችን ያለውን አሳዛኝ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ባለፈው ሳምንት በሃምሳ ገጽ ጽሁፍ የተቸው ዋና ጽ/ ቤት ኒውዮርክ የሚገኘው ሂውማን ራይትስ ወች የተባለው ድርጅት የአሜሪካን መንግሥት የሚከተለውን ፖለቲካ ጽናት አልባ መሆኑን ዘግቦ በአንድ በኩል የዚህ መንግሥት አምባሳደር ከተጨባጩ ሁኔታ ውጭ የኢህአዴግን ዴሞክራሲያዊነት ስ ‐ያሞካሹ በሌላ በኩል ደግሞ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዓመታዊ ሪፖርቶች ኢህአዴግን እየነቀፉ መጻፋቸው የአሜሪካንን ፖሊሲ በአንድ ራስ ሁለት ምላስ ነው በማለት ተችተዋል።

በዓለም የቀረችው አንድ ኃያል መንግሥት አፍሪካን ሳይቀር ድፍን ዓለምን በማላበስ ላይ ያለው ዴሞክራሲና የሰው ልጅ መብት መከበር ሂደት ለዚች ሃገራችን ብቻ ተነፍጎ ህዝባችን በጨለማና ጨካኝ አገዛዝ ውስጥ እየዳከረ ሲታይ በዓለም የቀረችው አንድ ኃያል መንግሥት ለምን በአንድ ራስ አንድ ምላስ መሆን አቃታት?

ሂውማን ራይትስ ወች ለዚህ የሚሰጣቸው ምክንያቶች ሁለት ናቸው። አንደኛው አሜሪካ ከኢትዮጵያ የምትፈልገውና በማግኘትም ላይ ያለችው የኢኮኖሚ ጥቅም ነው ካለ በኋላ በዚች ሕዝቧ በጭቆናና በድህነት በሚዳክርባት አገራችን ባለፉት ዓመታት ከመቶ ሃያ በላይ የአሜሪካ ኩባንያዎች ተተክለው ጥቅም እያካበቱ መሆኑን ድርጅቱ ዘግቧል። ሁለተኛ ምክንያት ብሎ የሚያቀርበው የስትራቴጂ ጥቅም ምክንያት ነው። እንደ ድርጅቱ አባባል አሜሪካ ኢትዮጵያን የሱዳንንና የሌሎች ሙስሊም አክራሪ ኃይሎች ግፊት ለመቋቋምና በሱማሊያና በአጠቃላይ የተረጋጋ ሁኔታ ለመፈጠር ልትጠቀምበት ትፈልጋለች።

የራሱን የኢኮኖሚና የስትራቴጂ ጥቅም አስቀድሞ መሥራት በየትም ያለ ነው። አሜሪካንም ሆነ ሌላ ባእድ መንግሥት የራሱን ጥቅም ፍለጋ እንጂ ለኛ ብልጽግና፤ ለኛ ልማት ብቻ ባህር አቋርጦ ይመጣል የሚል እምነት ሊኖር አይችልም። ይህ ያለ ነገር ነው። ችግር የሚመጣው አንድ ባእድ መንግሥት ይህንን የኢኮኖሚና የስትራቴጂ ጥቅሙን ሲያሳድድ በሚስተናገድበት ሃገር ላለው አሰቃቂ የህዝብ ሁኔታ እውር ነኝ ሲልና እንድያውም ከዚህም አልፎ ተርፎ የራሱን የኢኮኖሚና የስትራቴጂ ጥቅም ከሚስተናገድበት አገር ሕዝብ ጥቅም በላይ አርጎ ከጸረ ሕዝቡ መንግሥት ሲወግን ሲታይ ነው። ችግር የሚመጣው በአንድ በኩል ለሰው ልጅ መብት እቆማለሁ፤ ለደሞክራሲ እቆማለሁ፤ ለጋራ ጥቅም ለመተባበር መጥጫለሁ እየተባለ በሌላ በኩል ደግሞ በጸረ ደሞክራሲያዊነቱና በጸረ ሕዝብነቱ ምንም የማይወጣለት መንግሥት የጦር፤ የገንዘብ፤ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ድጋፍ በመለገሥ የህዝቦችን መከራ ማራዘሙ ላይ ነው።

የሆነ ሆኖ አሜሪካ በሃገራችን የምትከተለውን ፖሊሲ ይህ ዓለም አቀፍ ድርጅት በአንድ ራስ ሁለት ምላስ ብሎ አወገዘው እንጂ እኛ እንደዚህ አድርገን እስከዚህ ጸጉር ሰንጥቀን አናየውም። ለኛ ተጨባጩ ሃቅ አንድ ነው። ዛሬ ባለው ሁኔታ የአሜሪካ መንግሥት በሁለተኛው ምላሱ ኢህአዴግን ከአንገት በላይ ቢያወግዝም በተጨባጭ የዚህ አናሳና ጸረ ሕዝብ ኃይል ደጋፊ መንግሥት ነው። ከዚህ መራራ ሃቅ ቢነሱም ቅሉ ለዚህ ጭፍን ድጋፍ ዜጎች ሁሉ አንድ ምክንያት አይሰጡም። ብዙ ግዜ እንዳየነው ከሆነ ደጋግመው የሚቀርቡት ትንተናዎች ከሁለት ተከፍለው ሊታዩ የሚችሉ ናቸው።

በአንድ በኩል ኃያል መንግሥት የሚሉ ነገር ሲነሳ ጨርሶ የማይጥማቸው፤ ኢትዮጵያውያን ብዙ ናቸው። እነዚህ ወገኖች ይህ የአሜሪካኖች አካሄድ ራሱን የቻለና አላግባብ ጥቅም የመፈለግ ሎጂክ አለው ይሉናል። ዛሬ በሃገራችን በህዝብ የተጠላ፤ በተጭበረበረ ምርጫና ባነገበው ነፍጥ የሚገዛ፤ የዜጎችን መብት ይኸው ሪፖርት እንደሚለው "በዘልማድ፤ በየእለቱና በሰፊው" የሚደፍር አናሳ ኃይል እንደተጫነባት አሜሪካኖች አናውቅም ሊሉ አይችሉም። በህዝብ የተጠላ መንግሥት እስከሆነ ድረስ በሥልጣን ለመቆየት የነሱ የጦር፤ የገንዘብ፤ የፖለቲኪ ድጋፍ ስለሚያስፈልገው የግድ ለነሱ ታዛዥ መንግሥት ይሆናል። በዚህ ስልት የሚሄዱት ዜጎች ባጭሩ ለማለት የሚፈልጉት በህዝብ ፈቃድና ድጋፍ ተሰይሞ የሃገርንና የህዝብን ጥቅም ከሚያስከብርና ሊያስከብርም ከሚችል መንግሥት ከሕዝብ የየተለየና የተነጠለ ደካማ አሻንጉሊት መንግሥት ይበልጥ ይመቻል ነው። ከዚህም ተነስተው አሜሪካ ለኢህአዴግ የምትሰጠውን ድጋፍ አያዩትም።

በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች ዜጎች አሉ። አሜሪካኖች ፀረ ሕዝቡን ወያኔን የሙጥኝ ያሉት ከዚህ ኃይል ጋር መቀጠሉ እንደማያዋጣ፤ አለን የሚሉት የኢኮኖሚና የስትራቴጂ ጥቅም ቀስ በቀስ ወደ ትርምስ እየገባች በምትሄደው ሃገራችን ውስጥ ምንም ዘላቂነት እንደማይኖረው ያውቃሉ ባዮች ናቸው። የተረጋጋ ሁኔታና በህዝብ ድጋፍ የተደላደለ መንግሥት ቢኖርላቸው አይጠሉም። ነገር ግን ተቃዋሚ ነን የሚሉ ኃይሎች ተባብረውና ጥራት ባለው ሁኔታ ለኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ በዓለም ኮሚኒቲ ፊት ታዓማኒነት ያለው አማራጭ ማቅረብ አቅቷቸው ያማይጨበጥ ቆቅ ለሆነባቸው ደሞክራሲያዊ ነኝ ባይ ኃይል ሲሉ በእጃቸው ያለውን ፀረ ደሞክራሲ ዶሮ ሰደው ማሳደድን አልመረጡም ባይ ናቸው።

የኛ አስተሳሰብ ወደዚህኛው ያደላል። አንደኛ ነገር ዛሬ በዓለምና በተለይም ደግሞ በአፍሪካ እንደምናየው የቀረችው አንድ ኃያል መንግሥት በየደረሰችበት አናሳና ፀረ ሕዝብ መንግሥታትን ሥራዬ ብላ የመትከል ፖሊሲ አታካሄድም። ሕዝቦች እየታገሉና ድል እያደረጉ ደሞክራሲያዊ ሥርዓት በገነቡባቸው ሃገሮች በጋራ ጥቅም ላይ የተመረኮዙ ግንኙነቶችም ስትመሠርት ትታያለች። ሁለተኛ ነገር ደግሞ የኛም የራሳችን የቅርብ ልምድ አለ። የሰላምና እርቅ ጉባኤን ሃሳብ መጀመሪያ ላይ ተቃውሞ የነበረው የአሜሪካ መንግሥት

ተቃዋሚ ኃይሎችና ሕዝብ በአንድ ሆኖ ግልጽ የጋራ አማራጭ ሲያቀርብ ድጋፉን እንደሰጠ አይተናል።

ከዚህ ስንነሳ የምንደርስበት መደምደሚያ ግልጽ ነው። ኳሷ ያለችው እኛው ሰፈር ነው። ባእዳን ሰፈር አይደለችም። እንደዛሬ አራት አመቱ በጋራ ግልጽ የሆነ ዓላማ ይዘን ከተነሳን አሜሪካም ሆነች ሌሎች ባእዳን በአንድ ራስ አንድ ምላስ ሆነው የምናቀርበውን ሕዝባዊና ደሞክራሲ አማራጭ የሚደግፉበት ሁኔታ እንፈጥራለን። ይህንን ሳናደርግ ብንቀር ግን ከራሳችን ሌላ እንኳን ከባህር ማዶ የመጡ ባእዳንን ቀርቶ መልስ ዜናዊን እንኳን ማማረር አንችልም።

--------------////--------------

# ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ኬኒያ

የሕወሀት ኢህአዴግ መንግሥት ሃሳብን የመግለጥ መብት ለማፈን ሲል በኢትዮጵያ ለፃ ፕሬስ ላይ የከፈተው የአሳደህ አጥፋ ዘመቻ እየተባባሰ በመሄዱ በኬንያ ውስጥ ብቻ በስደት የሚኖሩ የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች ቁጥር ከቅርብ ግዜ ወዲህ ወደ ዘጠኝ ማደጉን ከስፍራው የደረሰን ዜና አስታወቀ።

በአሁን ግዜ በኬንያ በስደት የሚገኙ የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች፤

| | |
|---|---|
| መላኩ ፀጋዬ | ከ ሙዳይ |
| አቢይ አፈወርቅ | ከ ጠቋሚና ከፈታሽ |
| አንዱአለም መሃመድ | ከ ቅይጥና ከጣለወፍቅር |
| ወንድወሰን መለሰ | ከ ከታሪክ |
| ስለሺ ተገኔ | ከ ገሞራው |
| ስንታየሁ ቢሮ | ከ ትኩረት |
| ነጋ ታሪኩ | ከ ቅይጥ |
| ነጋ ገላሁን | ከ ማራቶን |
| ብርሃኑ ስየው | ከ ቅይጥ |

መሆናቸውን ስደተኞቹ ጋዜጠኞች ከናይሮቢ የላኩልን ደብዳቤ ይገልጣል።

በሕወሀት/ኢህአዴግ የማያቋርጥ የአፈና፤ የእስራትና የቅጣት በትር ተንገላተው በስደት ላይ የሚገኙት የኢትዮጵያ የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች ጠቅላላ ብዛት 24 ሲሆን የሚገኙትም በኬኒያ፤ በደቡብ አፍሪካ፤ በአውስትራሊያ፤ በኤውሮፓና በአሜሪካ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአሜሪካ የሚገኘው የነፃው ፕሬስ ጋዜጠኞች መብት አስከባሪ የሆነው ኮሚቴ ቱ ፕሮቴክት ጁርናሊስትስ ወይንም ሲ፤ፒ፤ጄ ባሠራጨው ዓመታዊ ዘገባው የመለስ ዜናዊ መንግሥት ጋዜጠኞችን በማሳደድና በማሰር ዘንድሮም ከሻምፒዮና አምባገነን መሪዎች መካከል አንደኛው ሆኖ መመዝገቡን አስታውቀዋል።